ቀን፡-26/05/2013

# <u>ለርዕሰ አድባራት ለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አባላትና ወዳጆች እንዲሁም በመላው ዓለም ለሚገኙ ኢትዮጵያውያን።</u>

## በስመ አብ፤ ወወልድ፤ ወመንፈስ ቅዱስ፤ አሐዱ አምላክ አሜን።

በአንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የአስተዳደር ጉዳይ ወሳኞቹ የቤተ ክርስቲያኗ ዋልታና ምሰሶ የሆኑት አባላቷ ካህናት ምእመናንና የሰንበት ት/ቤት ወጣቶች መሆናቸው በቃለ ዓዋዲውና በማንኛቸውም ሕገ ቤተ ክርስቲያን ላይ ተደንግጎ የሚገኝ ሆኖ ሳለ፤ አባ ግርማ ከበደና ተከታዮቻቸው ግን ይህንን ሃቅ በመካድ አዛዡም ሆነ ወሳኙ እኛ ብቻ ነን በማለት ሕዝብን ማማከርም ሆነ በሕዝብ ማስወሰን ሳያስፈልጋቸው በገዛ ፈቃዳቸው ቤተ ክርስቲያንን በመዝጋት በዓብይ ጾምና በሱባዔ ወቅት ሕዝበ ክርስቲያንን በመበተን ለከፍተኛ መከራና ችግር ዳረጉት።



አቡነ ገብርኤል

ይህ የእብሪት ድርጊታቸው አልበቃ ብሏቸው ደግሞ ቤተ ክርስቲያኗን በሃብትና በጉልበቱ ያቆመውን ሕዝብ በማግለል፤ የቤተ ክርስቲያኗን አቋም ከማይደግፉና ከማይከተሉ ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት እና ቃለ ዓዋዲም ሆነ የቤተ ክርስቲያኗ የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ በሚያዘው መሠረት ሳይሆን ርዕሰ አድባራት ለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ሳትሳተፍበት ተቋቋመ ከተባለው ሀገረ ስብከት ጋር በማበር ሁለት ጳጳሳትን (አቡነ ገብርኤል እና አቡነ ቀውስጦስ) ከኢትዮጵያ አስመጡ። የመጡትም ጳጳሳት በርዕሰ አድባራት ለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተፈጠርውን ትክክለኛ ችግር ሳይሆን ፍጹም ሃሰትና የፈጠራ ታሪክ እንዲነገራቸው አደረጉ።



አቡነ ቀውስጦስ



አቡነ እንጦንስ

ይህንንም መሠረት በማድረግ ይመስላል ሰላምና እርቅ ሊያወርዱ መጡ የተባለላቸው ጳጳሳት ከአቡነ እንጦንስ ጋር በመሆን፤ ለአንደኛው ወገን በማድላት ከለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን በአቋም የተለዩ አብያተ ክርስቲያናትን በመጠቀም በስብከትና በቅስቀሳ በቤተ ክርስቲያኗ ላይ ከፍተኛ ጫና ማሳደሩን ተያያዙት፡፡

በዚህ መካከል የፈጣሪ ፍቃዱ ሆነና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሕግና ሥርዓት እንዲሰፍንና የአባላት መብት እንዲከበር የሚታገለውን ሕዝብ የሚወክሉ ካህናትና ምእመናን፤ በቤተ ክርስቲያኗ ውስጥ የተፈጠረውን ትክክለኛ ሁኔታ አስመልክቶ ጳጳሳቱን በማግኘት ተገቢውን ገለጻ አደረጉላቸው። ጳጳሳቱ አስቀድሞ ከተነገራቸው ቁጥር ሥፍር የሌለው ውሸት ውስጥ አንዱና ትልቁ፤ የጸቡና ክፍፍሉ ሁሉ ምክንያት <u>**“ቤተ ክርስቲያኗን ኢትዮጵያ ከሚገኘው ቅዱስ ሲኖዶስ ገንጥለው በውጪ ለተቋቋመው ቅዱስ ሲኖዶስ ለማስረከብ በተነሱ ቡድኖችና ይህንን አናስደርግም በሚሉ መካከል የተነሳ ትንቅንቅ ነው”**</u> የሚል ነበር።

እዚህ ላይ አስገራሚ የሆነው ጉዳይ በውጪ የሚገኘው ቅዱስ ሲኖዶስ የአውሮፓ ሀገረ ስብከት ሊቃነ ጳጳስ አቡነ ኤሊያስን በመማጸን ለዲያቆን አባተ ጎበና ቅስና ከማሰጠት ጀምሮ (ለዚህ መረጃ በግጽ 3 ላይ አቡነ ኤሊያስ የጻፊትን ደብዳቤ ይመልከቱ)፤ በቅርብ ጊዜ ሳይቀር ኢትዮጵያ ያለውን ቅዱስ ሲኖዶስ የፓትሪያርክ ምርጫ ካካሄደ ለሁለተኛ ጊዜ ቀኖናን መጣሱ ነው በሚል ሲኖዶሱን የሚኮንን መግለጫ ማውጣታቸውን የዘነጉት አባ ግርማ ከበደና ተከታዮቻቸው (ይህ እነ አባ ግርማ ምእመኑን ሳያወያዩ ያወጡትን መግለጫ፤ በዚህ ኢሜል ተያይዞ/አታችድ ሆኖ ያገኙታል)፤ በዚህ ወቅት ደግሞ ራሳቸውን ኢትዮጵያ የሚገኘው ቅዱስ ሲኖዶስ ደጋፊና ተከራካሪ አድርገው በማቅረብ ቤተ ክርስቲያኗን ላለፉት 40 ዓመታት ጠብቆ ያኖረውና በደልና ጥቃት እየደረሰበትም ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኘው ቅዱስ ሲኖዶስ ጋር ያለውን መንፈሳዊ ግንኙነት ሳያቋረጥ በትዕግሥት ያሳለፈውን ሕዝብ ቤተ ክርስቲያንን የሚገነጥል ተደርጎ እንዲታይ የሚያደርግ የሃሰት መረጃ ለጳጳሳቱ መቅረቡ ነው።

በዚህ መሠረት ይህ በቤተ ክርስቲያኗ ውስጥ ከተፈጠረው ችግር ጋር ምንም ዓይነት ቀጥተኛ ግንኙነት የሌለው የሲኖዶስ ጉዳይ አባ ግርማ ከበደና ተከታዮቻቸው በሃሰት መረጃነት ቢያቀርቡትም በውጪ ሃገር የሚገኙና ስደተኛው ጥሮና ግሮ ያቋቋማቸውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት ሙሉ በሙሉ በመቆጣጠር በደጋፊዎቹ ለመሙላት ፓለቲካዊ ዓላማ ይዞ የሚንቀሳቀሰው የኢትዮጵያው አገዛዝ ዕቅድ አካል ስለሆነ፤ የጳጳሳቱ ተልኮም ይህንኑ ለመፈጸምና ለማስፈጸም በመሆኑ የሃሰትም ወሬ ተነጋራቸው እውነቱን እንዲረዱት ተደረጉ በቤተ ክርስቲያኗ ውስጥ የተፈጠረው የሰላም መናጋትም ሆነ በሕዝበ ክርስቲያኑ መካከል የተከሰተው መከፋፈል ሳያሳስባቸውና ሳያስጨንቃቸው ከዛ ይልቅ ይዘውት የመጡትን ዓላማ በማስፈጸሙ ላይ ብቻ በማተኮር ቀጥሎ የተመለከቱትን ተግባራት አከናውነዋል።

1. ለጳጳሳቱ ገለጻ እንዲያደርጉ ሕዝብ ወክሎ የላካቸው ካህናትና ምእመናንን ካነጋገሩና እውነታውን በሚገባ የመረዳት ዕድል ካገኙ በኋላ፤ እውነታውን መሠረት አድርገው ስለ ሰላምና እርቅ በማሰብ ፋንታ፤ በልዑካኑ ውስጥ የተካተቱን ካህናት እናንተ ከምእመኑ ጋር

ባትወግኑ ኖሮ ምእመናኑ ብቻቸውን እዚህ ደረጃ መድረስ አይችሉም ነበር በማለት በምእመኑ ፊት በካህናቱ ላይ ከፍተኛ ጫና ያሳደሩ ከመሆናቸውም በላይ፤ እጅግ በሚያስገርም ሁኔታ ምእመን የተባለ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከቁጥርነት ያለፈ በራሱ ዓዕምሮ ተመርቶ አንዳችም ነገር የመወሰን አቅምም ሆነ መብት የሌለው አድርገው የሚቆጥሩ መሪዎች መሆናቸውን በገሃድ አረጋግጠዋል።

2. አባ ግርማ ከበደና ተከታዮቻቸው ባስነሱት ሁከትና ረብሻ ምክንያት በሕዝብ መካከል ጸብና መከፋፈል ተፈጥሮ ጳጳሳቱ ይህንን ጸብና ክፍፍል በማጥፋት ሰላምና እርቅ እንዲሰፍን ለማድረግ የተከፋፈሉትን የቤተ ክርስቲያኗን አባላት በስማቸው ጠርተው በማስታረቅና በማስማማት እግዚአብሔር የሚወደውን ተግባር ከማከናወን ይልቅ እነሱ ግን ያደረጉት፦

   2.1 የቤተ ክርስቲያኗ አገልጋይ የሆኑና በተለያየ ምክንያት ከቤተ ክርስቲያኗ የተገለሉ፤ እንዲሁም የሌላ አብያተ ክርስቲያናት አገልጋይ ካህናትን ብቻ በጋራና በተናጠል ሰብስበው በማነጋገር፤ ለቤተ ክርስቲያኗ ችግር መንስዔም ሆነ መፍትሔ ያልሆነውን ርዕሰ አድባራት ለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ኢትዮጵያ በሚገኘው ቅዱስ ሲኖዶስ እና በሰሜን ምዕራብ አውሮፓ ሀገረ ስብከት ሥር ነች በማለት እንዲያረጋግጡ ብቻ ሳይሆን ልክ እንደ ጉዳይ አስፈጻሚ ጠበቃ እያንዳንዱን ካህናት በውሳኔው ላይ ሲያስፍረሙ ከርመዋል።

   2.2 ጳጳሳቱ ጸብና መከፋፈል ደርሶባቸዋል የተባሉትን የርዕሰ አድባራት ለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን አባላትን ለሰላምና እርቅ ጉባኤ ከመጥራት ይልቅ፤ በቤተ ክርስቲያኗ ውስጥ የተፈጠረውን ችግር የቤተ ክርስቲያኗን አስተዳደርም ሆነ ሃብትና ንብረቷን ጭምር ሙሉ ለሙሉ ለመቆጣጠር ጊዜው አሁን ነው በሚል ይዘውት የመጡትን ዓላማ ለማሳካት፤ የእርቅና የአንድነት ጉባኤ በሚል በ19/05/2013 የቅድስት ሥላሴ፣ የቅዱስ ገብረኤልና የጸራ ጽዮን አብያተ ክርስቲያናትን አባላት በመጥራት የቤተ ክርስቲያኗ አባላት ያልሆኑ የሌሎች ቤተ ክርስቲያን አባላት በቤተ ክርስቲያኗ የውስጥ ጉዳይ ላይ አቋም እንዲወስዱና እንዲወስኑ አስደርገዋል።

   በዚህ ስብሰባ ላይ እንደታየው አሁንም ጳጳሳቱ ያስነበቡት ውሳኔና መግለጫ የካህናቱን ብቻ ሲሆን፤ ምእመኑ ግን ያንን ሰምቶ ከማጨብጨብ በስተቀር አንዳችም አስተያየት የመስጠትም ሆነ የውሳኔ ሃሳብ የማቅረብ መብት እንደሌለው በማሳየት፤ ካህናትን ካልሆነ በስተቀር ምእመናን በቤተ ክርስቲያናቸው ጉዳይ የመወሰንም ሆነ ሃሳብ የመስጠት ምንም ዓይነት መብትና ሥልጣን የላቸውም ብለው የሚያምኑ ሥለመሆናቸው በድጋሜ አረጋግጠዋል።

   **ይህ ጳጳሳቱ ከኢትዮጵያ ድረስ መጥተው የፈጸሙት ተግባር ሰላምና እርቅን የማስፈን ተግባር ነው ከተባለ የተጣሉ ባልና ሚስትን ለማስታረቅ ሽማግሌ ሆኖ ቀርቦ ባልና ሚስቱን ትቶ ጎረቤቱን ሁሉ ሰብስቦ፤ በባልና ሚስቱ የጥል ጉዳይ ላይ ጎረቤቱ ውሳኔ እንዲያሳልፉ በማድረግ ባልና ሚስቱን አስታረቅን እንደማለት የሚቆጠር ብቻ ነው።**

3. ጳጳሳቱ በድርጊታቸው በመቀጠል፤ አንዳችም የምእመናን ተወካይ ሳይኖር ሦስት ካህናት ብቻ ይቆጣጠሩት የነበረ የሰበካ አስተዳደር ጉባኤ በአንድ ጊዜ ከ15 በላይ የሚሆኑ ምእመናንን ቤተ ክርስቲያን ቅጥር ግቢ ውስጥ እንዳትደርሱ በማለት በጸጥታ ኃይሎች ለማባረር ሙከራ አድርጎ በዛ ሳቢያ ከፍተኛ ሁከት መፈጠሩንና ከዛም በኋላ አባላት ቃለ ዓዋዲው፣ የቤተ ክርስቲያኗ የውስጥ መተዳደሪያ ደንብና የቻሪቲ ሕግ በሚፈቅድላቸው መሠረት ተሰባስበው፤ ከካህናት 4 ከምእመናን 4 እና ከሰንበት ት/ቤት ወጣት አንድ፤ በድምሩ ዘጠኝ አባላትን የያዘ የሰበካ አስተዳደር ጉባኤ መርጠው መሰየማቸውን ጳጳሳቱ በሚገባ እያወቁ፤ ከነ አባ ግርማ ከበደና ተከታዮቻቸው ጋር በማበር ሕጋዊነት የሌለውን የሰበካ አስተዳደር ጉባኤ ሕጋዊ ሰበካ አስተዳደር ጉባኤ በማስመሰል በ26/05/2013 በርዕሰ አድባራት ለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ስም የአስቸኳይ የሰበካ ጠቅላላ መንፈሳዊ ጉባኤ እንዲካሄድና እነሱ ባሉበት አዲስ የሰበካ አስተዳደር ጉባኤ ምርጫ እንዲካሄድ ጥሪ በማስተላለፍ ላይ ይገኛሉ።

ሕዝበ ክርስቲያን ሆይ፤ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖታችንና ቤተ ክርስቲያናችን ብለን ለዓመታት ጥረንና ግረን በእግዚአብሔር ተራዳኢነት ያቆምናትን ቤተ ክርስቲያናችንን ለትውልድ የምትተላለፍ ቅርስ፣ ትንሿ ኢትዮጵያችን ብለን ገና ደስታችንን ሳናጣጥም፤ ዛሬ ቅዱስ ሲኖዶስና ሀገረ ስብከት በሚል ሽፋን በቤተ ክርስቲያናችን አስተዳደርም ሆነ በሃብትና ንብረቷ አዛዥ እኛ እንጂ እናንተ አይደላችሁም በሚሉ ተቀናቃኞች እየተከበብን እንገኛለን።

ከዚህ መውጫው መንገድ በቁርጠኝነት ተነስቶ ሕጋዊ መብትንና ባለቤትነትን ማስከበር ነው። በመዘናጋት፣ በስንፍናና በየዋህነት መብትን አሳልፎ ሰጥቶ ቤተ ክርስቲያንን የዘረኛ አገዛዝ ሥርዓት አራማጆችና ደጋፊዎች ንብረት እንዳትሆን መጠበቅ የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ግዴታ ነው። በዚህ መሠረት ለእውነትና ለፍትሕ ቆሜአለሁ የምትሉ በስደት ላይ የምትገኙ ኢትዮጵያውያን ሁሉ፤ ነገ ዛሬ ሳትሉ ርዕሰ አድባራት ለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያንን ለማዳን የሚደረገውን ትግል በመቀላቀል አቅምአችሁ የፈቀደውን ሁሉ አስተዋጽኦ እንድታደርጉ ጥሪ እናስተላልፋለን።

**ወስብሐት ለእግዚአብሔር! አሜን!!**

በስዊድን የኢትዮጵያ
ኦርቶዶክስ ትዋሕዶ
ቤተ ክርስቲያን
መንበረ ጵጵስና

ETHIOPIAN ORTHODOX CHURCH IN SWEDEN

ደብረ ሰላም
መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን

ETIOPISKA
ORTODOXA TEWAHEDO
KYRKA ÄRKESTIFTET
I SVERIGE

ሚያዝያ ፳፯ ፪ሺህ ዓ.ም
April 04/05/2013
ስቶክሆልም ስዊድን

በለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ማኅበረ ምእመናን በሙሉ።

በመጀመሪያ እግዚአብሔር አምላክ እንኳን በሰላም ጠብቆ ለብርሃነ ትንሣኤው አደረሳችሁ። በዚህ ዓመት በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ወርኃ ጾም ቤተ ክርስቲያናችን እጅግ የተፈተነችበት ወራት ነበር። ቤተ ክርስቲያናችን የተፈተነችበት ነው ስንልም ምእመናኑ በከባድ ፈተና ላይ የነበሩበት ወራት መሆኑን እናንተ ብቻ ሳትሆኑ በመላው ዓለም ያሉት ክርስቲያኖች ሁሉ የተረዱት ነው። ይህ ዓይነቱ ፈተና በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ደርሶ ባያውቅም ቤተ ክርስቲያናችን ግን ፈተና ተለይቷት አያውቅም። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች የላከላቸው የማጽናኛ መልእክት እንዲህ የሚል ነበር፤ ለሰው ሁሉ ከሚሆነው በቀር ምንም ፈተና አልደረሰባችሁም ነገር ግን ከሚቻላችሁ መጠን ይልቅ ትፈተኑ ዘንድ የማይፈቅድ እግዚአብሔር የታመነ ነው። ትታገሱም ዘንድ እንድትችሉ ከፈተናው ጋር መውጫውን ደግሞ ያደርግላችኋል። 1ኛ ቆሮ 10፥13
በለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን መዘጋት ጉዳይ ያላዘነ የለም። እኔም በበኩሌ በጣም ያዘንኩ በመሆኑ ከኃዘኔ የተነሣ ስለ ለንደን ቤተ ክርስቲያን ለሚጠይቁኝ ሁሉ መልስ የምሰጠው በብስጭትና በቁጣ ነው። ይህ ቤተ ክርስቲያን ስለመዘጋት ጉዳይ ለአባ ግርማም ሆነ ለቄስ አባተ ደውዬ ጉዳዩ ለወደፊት እንዴት ነው ብዬ አማክሬአቸው ነበር።
በመሠረቱ አባ ግርማ ቄስ አባተን ባለፈው ዓመት ቅስና እንድሾምላቸው ወደኔ ልከውት የቅስና ማዕረግ የተቀበለ ነው። ይህም ስለሆነ እነዚህ አባቶች ሰላም ቢፈልጉ ኖሮ እኔን አስታርቀን ብለው ይጠይቁ ነበር።
ስለዚህ አሁንም የማሳስባችሁ ሰላም እስከሚገኝ ድረስ ቤተ ክርስቲያናችሁን በተጠንቀቅ እንድትጠብቁ አደራ እንላለን። አሁንም ቢሆን ከጎናችሁ ስለሆንኩኝ ከአባታዊ ጸሎቴ በተጨማሪ በሐሳብና በምክር ልረዳችሁ ዝግጁ ስለሆንኩኝ በማንኛውም ሰዓት ብትጠሩኝ ለመምጣት ፈቃደኛ ነኝ።
ከዚህ በተረፈ የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ በዓለ ትንሣኤ የሰላምና የደስታ በዓል እንዲሆንላችሁ በዓለም ዙሪያ ያለው ሕዝበ ክርስቲያን ሁሉ ጸሎት ነው።

አባ ኤልያስ በአውሮፓና በምሥራቅ አፍሪካ
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ

አባ ኤልያስ ሊቀ ጳጳስ
ABBA ELIAS
ARCH BISHOP


| Ärkebiskop Elias | Telephone | Kyrkans Besöksadress | Telephone | Postadress | Postgiro | Orgnr |
| --- | --- | --- | --- | --- | --- | --- |
| Gillerbacken 26 1tr | 08-7492928 | Pålsbodagränd 3 | 08-7246076 | Box 1036 | 4980549-2 | 252002-8859 |
| 124 64 BANDHAGEN | | Hagsätra centrum | | 101 38 STOCKHOLM | | |